# ከ የዛሬዪቱ ኢትዮጵያ እና ከ የኢትዮጵያ ድምፅ ጋዜጦች ተገልብጠው የተተየቡ የገጣሚና ሰዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታ ግጥሞች (መስከረም 1947 – ነሐሴ 1961)

**በፈቃደ አዘዘ**

## ሞኜ ተላሌ

በአራት እግሩ ሲሔድ ሲቆም በሁለቱ
ሲያጌጥ ሲለባብስ የሰው ልጅ ኩራቱ::
ይኖር ይመስለዋል ዓለም እንዲህ ጣፍጣ
መድከም መንገዳገድ እርጅና ሳይመጣ::
ወዙ ሲያብለጨልጭ ፈገግታው ሲያበራ
"ሰው እኔ ነኝ እኮ ማን አለ ጠንካራ"
ብሎ ሲደነፋ ቆሞ ሲንጠራራ::
ፍፁም አያስብም ሰዓቱ ሲቆጥር
ነገ ዛሬ ሆኖ ወደትናንት ሲዞር::
ቀድሞ አይሰማውም ደቂቃው ማለፉ
ቀኑ መሽቶ ነግቶ ሲለፈልፍ ወፉ ::
ዛሬ እኮ ዛሬ ነው ነገም ቢሆን እሱ
ከእድሜው ላይ አንድ ቀን ሁለት መቀነሱ ::
"ይህ እርጅና አይደለም ዛሬ ጤናማ ነኝ"
"ተመልከት ጡንቻዬን ዝለል ብረር ሲለኝ"
ነገ ሃያ ዘጠኝ በዓመቱም ሠላሳ፤
"አበድክ ጤናም የለህ ገና ነኝ ጎልማሳ"
ሠላሳውም አልፎ አርባ ዓመት ሲሆነው
ቁጭ በል ተጫወት ይቅርብ ሩጫው::
"ማሞ መስታዎቱን እስቲ ወዲህ ስጠኝ"
"ከሽበቱ በቀር አሁንም ወጣት ነኝ"
አምሳም ሥድሳም አልፎ ዘጠና ቢሞላ
ሞኝ ነው የሰው ልጅ ማሙዬ ተላላ::
ዕድሜ እያሳቀቀው እርጅና ቤት ገብቶ
ዞር ብሎ ሲያስተውል ያንን ዳገት ወጥቶ
መርበትበት መደንገጥ ያኔ ነው ሐዘኑ
"ይገርማል ይደንቃል እንዴት ሔደ ቀኑ፤"
ሁሉም አዲስ ነገር አይቶ የማያውቀው
ከቶ ምን ልብስ ነው ሳያውቅ ያጠለቀው፤
ወህ ውስጥ ቆይቶ በሳት የተቆላ
ቆዳው ተጨማዶ ሲመስል ባቄላ፤
ጅማቱ ሲታሰር እግሩ መሔድ ሲተው
እጁ ሲንቀጠቀጥ መጨበጥ ሲያቅተው፤
ዓይኑ እየደከመ ጆሮው ሲያወላውል
አንሱኝ ብድግ አርጉኝ ያዙኝ እቀፉኝ ሲል፤

እንዳያፍር ሲባል እንዳይወድቅ ሲጠገን
ሕልም እየሆነበት የበረረው ዘመን፣
ለፅድቅ ነው ብሎ ሞት መጥቶ ሲያነሳው
ሰው ያብዳል ይጮኻል ያለቅሳል በሬሳው፣
ካለመኖር መጥቶ እኖራለሁ ይላል
ሲሞትም በኋላ ቆይቶ፣ ይነሣል፣
መኖር የሚሉትን ይኸን ቃል ቢያገኘው
መንካትም መዳሰስ መጨበጥ ቢቻለው፣
እንደብር በኪሱ ወይ እንደቀለበት
እጣቱ ላይ አርጎ መኳተን ይብዛበት?
ማ መሆኑን ሳያውቅ ራሱን ሳይገምት
እንደጥንግ ለግተው ወደላይ የጣሉት፣
አየር ላይ ተንሳፎ የሚይዘው ሲያጣ
ባክኖ ተሽከርክሮ ዞሮበት ሲመጣ፣
በስስታምነት ራሱን ያኮራል
"እግዜርን አየሁት ልክ እኔን ይመስላል"
እሱ ለዚህ ዓለም ቅንጣት ኢምንት ነው
ይህ ዓለም ለዚያኛው ያኛው ለወዲያኛው
ተያይዞ ሲሔድ መጨረሻም የለው::
የአእምሮው መብራት እያነሰ ኃይሉ
እየረቀቀበት ሲጠፋበት ውሉ::
ጭጋግ እየሆነ ምሥጢሩ ሲሳነው
ካለመኖር ፈጥሮ መሬት ላይ የጣለው
እንቆቅልሽ ሆኖ ዝም ብሎ የሚያየው::
ማነው፣ ምን ነው፣ የት ነው፣ እንዴት ነው ከማለት
ሲሔድ ያገኘዋል በቀጠሮው ሰዓት::
ሳር መሳይ ጎዝጉዞ ካሳለፈ እንቅልፉን
ባይለብስስ ባያጌጥ ቢሆን ራቁቱን ::
ፀሐይ ስትገባ ካየ ስትወጣ
ወሀ ከወንዝ አፍሶ በፍኙ ከጠጣ::
ተገዢ ከሆነ ሥራውን ከሠራ
ሓሳቡን ሳያውቀው በሌላው ሲመራ::
አለ ብሎ ቆርጦ የለም ብሎ ካለ
በሁለቱም ቆሟል መንገድ መች ቀጠለ
እንጀራና ወጡን ደጎና አርጎ ከበላ
ሰው እኮ ከብት ነው አይ ሞኜ ተላላ::

# ትዝታ

ልሒድ ልብረር ልውጣ ይውሰደኝ ንፋሱ
አሞራን ልከተል አልለይም ከሱ
ዳመናውን ልልበስ ልሸፈን ይብረደኝ
ወሀ ሆኖ ጠፍቶ ፀሐይ እስኪፈጀኝ
ልንሳፈፍ ባየር ላይ ልመልከት መስኮችን
በያይነቱ አበቦች ቀያይ ቢጫዎቹን
ወንዞቹን ልያቸው እጥፍ ዘርጋ ሲሉ
ተራራን ሰንጥቀው ሲያልፉ በማህሉ
እግሬ አፈሩን ይርገጥ ልምጣ መሬት ልንካ
ዛፍ እንጨቱን ልየው እልም ባለ ጫካ
እንቅፋትም ይምታኝ እሾህ ይውጋው እግሬን
ከእንቅልፌ እንድነቃ እንዳውቀው መኖሬን
ልውደቅ ልንከባለል ልብሴን አፈር ይንካው
ድጡ ላይ ልንሻተት ያበላሸኝ ጭቃው
ልምቦጫረቅ ልግባ ወሀ ውስጥ ልዋኝ
ዓሣን ልምሰለው ጎርፉ ይውሰደኝ
እግሬን ላፈራርቀው እንደዕንቁራሪት
ላድንቅ ላስተውለው ያላትን ብልሀት
ውሀው ሰውነቴን ያርስ ያለስልሰው
ፏፏቴው ያጓራ ያንሳፈኝ አረፋው::
ተወርውሬ ልውጣ ባሸዋው ላይ ልሩጥ
የእግሬን ምልክቶች ልተው መሬቱ ውስጥ
ትንፋሼ ይቆረጥ ፍጥነቴን ልቀጥል
ነፋስ ቡቃያውን ልየው ሲያመሳቅል
በተራ ሲያስተኛው አጥፎ ሲዘረጋው
ማዕበል አስመስሎ እየቆራረጠው
የታጨደው ክምር ፈርሶ ሲንገላታ
አየር ላይ ሲወጣ ባውሎ ነፋስ ዋልታ
ልስጠም ልውደቅበት ፍራሽ ይሁን ሳሩ
መዓዛው ይሸተተኝ ልምላሜ ማሩ
እዛፉ ጥላ ስር ይለፍልኝ ቀኑ
ልስማ ላንቀላፋ ወፎቹ ሲዘፍኑ
እረኛው ሲዘምር ሲያሞግስ ከብቶቹን
ወዲያ ማዶ ደግሞ ጋራው ጥላ ሲሆን
አረሁ ሲደበቅ ሜዳው ሲኾጎረጎር
ዛፉ እየጠቆረ ከሩቅ ያለው መንደር

በጭስ ተሸፍኖ መልኩን እያሳሳ
ውበት ማታ መጣች የቀኑን ጩርሳ
ፀሐይ የሞቀውን ተጎናፅፋ ልብሷን
ቀላ ባለ ብጫ ሸፍናው ፍጥረትን
ስትሔድ ስታሾልቅ ስትዘቀዘቅ
እነሆ ጌጦቿ አልማዝና ወርቅ።
መሬት ሲቀዘቅዝ ሲፈካ ቀላዩ
ጨረቃና ኮከብ ባንድ ላይ ሲታዩ
ፊቴን ሲዳብሰው ቀዝቃዛው ሽውታ
ሰውነቴን ትቼ እስቲ ልረፍ ማታ
ጠቅላላ ኑሮዬን በዕለት ሞት ልሻረው
ልቤ ከበሮውን በዝግታ ይምታው
ሓሳብና ድካም እኔን መጥተው ይጡ
ሥጋዬ ውስጥ ገብተው ፈልገውኝ ይውጡ
የተሸሸገውን ሀብቴን እንዳይሰርቁት
ሌቦቹ ቆፍረው ሳይከፋፈሉት
መላእክት ይምጡበት ሳጥናኤል ይሸሽ
ትጠበቅ ትዝታ እንዳትበላሽ።
እልቤ ውስጥ ገብታ ትታሸግ በቁልፍ
ባንጎሌ ብራና ዜናዋ ይፃፍ
በቀለም ያበደች ኃይሏ የደመቀ
በዘፈን በዜማ የተብረቀረቀ
የደሜ ሕዋስ ነች ላፍንጫዬ ሽታ
ባፌ ጣሟ ማር ነው የመንፈስ ፀጥታ
የሙዚቃ ስልቷ የጆሮዬ ፀጋ
ያይኔ ውበት ቀለም የሰውነቴ አልጋ
የልጅነት ጊዜ ትምጣ ትዝታዬ
ዱሮ የተሠራች አሁን መኖሪያዬ
የወደፊት ተስፋ መልኳ እማይለወጥ
ተቀርፃ የምትኖር በሰውነቴ ውስጥ።

# መታሰቢያ

በእጅ ላይ የሚውል የጣት ቀለበት
ባንገት የሚደረግ ወይም በደረት፤
በወርቅ የሰከረ ባልማዝ ልቡ ጠፍቶ፤
ስም የተፃፈበት ሰጭን ለማስታወስ
እጅ የሚዳብሰው የሚቀመጥ በኪስ፤
የሚሰስትለት የሚሆን ለጌጥ
መንፈስ የሚወደው ሞገስ የሚሰጥ
በጣም የሚደነቅ ሥራው የረቀቀ
ይኸ መታሰቢያ ነው ጠፍቶ ካልወደቀ::
ሲቀመጥ የሚያምር በጠረጴዛ ላይ
ክቡር ድንቅ የሆነ ጧት ማታ የሚታይ፤
ያበባ ማኖሪያ ገፀበረከት
የሚያማምር ኀረግ የተጣለበት
የወዳጅ ስጦታ ወይም ፎቶግራፍ
ለልጅ ልጅ የሚሆን የሚተላለፍ፤
ቤት ካልተቃጠለ ሌባ ካልሰረቀው
ወይ ካልተቀደደ ሕፃን ካልሰበረው
የሩቁን ያቀርባል ይኸ መታሰቢያ ነው::
በደምብ የታሰረ ቀይ ክር ያለበት
በሳጥን የሚኖር የፍቅር ወረቀት፤
"አትርሱኝ" የሆነ የፀጉር ጉንጉን
አስታዋሽ ፈላጊ ጥንት የቀረውን::
ቁልፍ የሚጠብቀው ባመት የሚወጣ
ልብስና መሀረም የሚኖር በሻንጣ፤
ጫማም የውስጥ ልብስ ትኒኒሽ ስጦታ
ለጊዜው ያጠግባል ሲታይ በደስታ፤
ነጋሪ ይሆናል ብል ካላነተበው
ያለፈውን ጊዜ መልሶ ሲያመጣው::
ቁልፍ የማይደብቀው መታሰቢያ ሞልቷል
በግልፅ እየታየ ሊሰወር ይችላል፤
ሳጥን መክፈት የለም ወረቀት ማንበብ
ቦታው ማከማቻው ማደሪያው ነው ልብ፤
ብርሃን አያሻውም ጨለማ አይጋርደው
ጊዜ አይለውጠውም ዓይን እንኳን ባያየው፤
ልስልስ ጣፋጭ ጥፊ ጉንጭ ላይ የሚያርፍ
"እወድህለሁኝ" ብሎ ሲጋረፍ
የሚያማምረው ጣት ፍፁም አይረሳም

ወረቀት በመፃፍ ዝብዝበ አያሻም፡፡
ወይም አለ ቁጣ ውስጡ የውሸት
ፈገግታን የሚሰጥ ሲያሰላስሉት፣
ወዲያው ተለውጦ ደግሞም በመሳቅ
አፍን ከፈት አርጎ ከንፈርን ለቀቅ፣
ጥርስን አሳይቶ ፈዞ በማስተዋል
ከንፈርን ከከንፈር አምጥቶ በማዋል፣
ሙዚቃው ሲዘፈን ቀዩ ብርሃን በርቶ
ዳንሱን ሲራመዱት በጣም ተጠግቶ፣
ጆሮን ሲማርከው ቀስ ያለው ንግግር
መታሰቢያ ይኸ ነው የማይበላው አፈር፣
ሁኔታው ጊዜውም ቦታው ተጨምሮ
አስታዋሽ በመሆን የሚኖር ነው አብሮ፣
በፍፁም አይዝግም አያረጅ ቢቀመጥ
እያሸበረቀ ጊዜው ሲለዋወጥ፣
ካንጎል አይፋቅም በአእምሮ ተፅፎ
ሲታወስ ይመጣል ብዙ ዘመን አልፎ፡፡
መታሰቢያ ይኸ ነው የተሠራ በጥንት
ሥጋ የመረገው ያጣበቀው ጅማት፣
ቆዳ ያለበሰው በደም የተቀባ
ነፍስና አካል ሆኖ በሰው የሚገባ፡፡

# ጦርነት

ያዘቀጠው አሰር እየደፈረሰ
የተቀጣጠለው እንጨቱ እየጨሰ
መሬት ቁና ሁና የሰው ልጅ ሲጨንቀው
እሳት ተያይዞ አገሩን ሲያለብሰው
ባለቤት ተሰዶ አዱኛ ፈራርሳ
አሞራ ሲያንዣብብ ተከምሮ ሬሣ
ሥጋ ሲርበደበድ ነፍስ ይሸቆጠቆጣል
የኔ እያቀዘፈው ደም ይገነፍላል።
ኮሽ ባለ ቁጥር ዞሮ ሲገላመጥ
እየተንሻተተ ገደሉን ሲባጥጥ
ሲቃትት ሲደክም ሲርበው ሲጠማው
ሥጋውን በመካድ ሞትን ይመኛል ሰው።
የፍቅር ጥላነው ጭጋግ የደስታ
ኀዘን መንገላታት፣ መታሠር መቸገር
መቁሰል መሰቃየት የሌለው ፀጥታ
ያንድነት እከክ ነው ልብሱ የነተበ
በላብ በጭቅቅት ገላው የረጠበ
ተለዋዋጭ መልኩ ያልታወቀ ግቡ
አልቋል ሞቷል ሲሉት ያው ይነትራል ልቡ።
ሥጋ ተለያይቶ ሲቀር አጥንታቸው
ማንንም በስሙ መጥራት የማንችለው
መልካቸው ሲጠፋ ሁነው እንዳልነበር
እነሆ ርስታቸው የእኩል ቤት መቃብር።
መድፍ የተከላቸው መትረየስ ዘርዝሮ
ቦምብ የመገባቸው አይሮፕላን በሮ፣
ታንክ በደነጎረው ጠመንጃ ዘርቷቸው
ጢስ ወሀ እየሆነ ሲጠጡ ባፋቸው
የታል የበቀሉት ወዴት ነው ቦታቸው?
ልምላሜአቸው የታል ፍሬያቸው የታለ?
ሐውልቱ ድንጋዩ ምን አጎነቆለ!

    ባንድ በኩል ደግሞ
    የሰላም ሚዛን ነው፣
    የበዛን አረሞ
    የሚያስተካክለው።

ሰላም ብዙ ሲቆይ ሥሩ ይሻግታል
መሠረቱ ዝጎ ቀስ ብሎ ይወድቃል፣
አንስቶ በመካብ የፈራረሰውን
ቀብሮ በመለሰን ሲያድስ መሠረቱን፣

ኃይለኛ ሲገባ ሲከተል ዓላማ
ባላህ እርጋ ብሎ አዋጁን ሲያሰማ፤
ይኸው ተጀመረ አዲስ ዓይነት ሰላም
ዳገመኛ እስቲወድቅ ፈርሶ እስቲደመደም፤
ሰላም ያቻት ብሎ ሁሉም የሚጮኸው
ክፉ ቀን አታምጣ ብለን የምንተቸው፤
በፀሎታችን ውስጥ መሪ እንዳያሳጣን
ወድቀን እንዳንቀር ተገዥ በመሆን፤
ያቻት ዓላማችን ነፋስ ተቀበላት
ብለን የምንቆመው ሰላም የምንላት
ፀጥታ ሲኖር ነው አልፈን በጦርነት፤
አንደኛው ሲተኛ ያኛው ሲጠብቀው
ሰላም ወይ ጦርነት ድርና ማግ ናቸው።

# ስኳር

ዱሮ ከውጭ አገር ዘንድሮ ተወንጂ
ስኳር እያስመጣ ነግዷል ፈረንጅ
በእጃችን ከገባ መኪናው ከመጣ
ሸንኮራው ይጨመቅ ነጩ ስኳር ይውጣ፡፡

*     *     *     *     *     *

# የሴቶች መሻሻል

ከብዙ ቀስማለች ሰፊ ነው ትምርቷ
እንዴት ያምርባታል ቀለም ባንደበቷ፡፡

# ምንድን ነሽ?

ነፋስ ወይም አየር ወሀ ነሽ እንፋሎት
መልአክ ወይም ሰይጣን ብርሃን ወይም ጽልመት?
ድንጋይ፣ አፈር፣ ጭቃ፣ ቅጠል፣ እንጨት፣ ልጥ
አልተረዳሁትም ሥራሽን በቅጥ።
ብረት፣ ነሐስ፣ መዳብ፣ ወርቅ፣ ሉል፣ አልማዝ፣
አገልጋይ ለሥራ ለጌጥ የሚያዝ?
ቀይ ነሽ ብጫ ነሽ፣ አረንጓዴ ጥቁር
ሐምራዊ ቡና ዓይነት ቀለምሽ የሚያምር?
ፉንጋ ነሽ ሰልካካ ቆንጆ ወይም መጥፎ?
የማር እንጀራ ነሽ የወጣ ከቀፎ።
ወለላው በጌሾ በውሀ ተጣርቶ
ናላዬን ያዞረው ከቦታው አናግቶ።
አጭር ነሽ እረጅም ወፍራም ወይ ቀጭን?
ወርድና ስፋትሽ ልኩ ምን ይሆን?
እያለሽ የለሽም ሳትኖሪም አለሽ
ጣፍጠሽ የምትመሪ ማርና እሬት ነሽ
የምታቃጥዪ ቃሪያ ነሽ በርበሬ
እሳት ለብላቢ ነሽ አከሰልሽኝ ዛሬ።
ነገ ስትሄጂ የለሁም ትቢያ ነኝ
ካንቺ ጋር ይጓዛል ሐሳቤ ሳይገኝ።
እርግጥ የፈጣሪ ነሽ ወይ እስትንፋስ?
እውነት ቀሪ ረቂቅ የማይዳሰስ
ኃይሌ ነሽ ምርኩዜ ብርታቴ ጤናዬ
ጠጉሬ፣ ግንባሬ ዓይንና አፍንጫዬ።
አፌ ጆሮዬ ነሽ ጥርሴና ምላሴ
ሆድ ዕቃዬ ልቤ ሳምባዬ እስትንፋሴ።
አንጎሌ ነሽ አንቺ የግሬ የጄ ጌታ
ደግፈሽ የያዝሽኝ የሆንሽኝ መከታ።
አልጋሽ ነኝ፣ ፍራሽሽ፣ መከዳ ልብስሺ
የምትዳስሺኝ ስትንቀሳቀሺ።
ጥላሽ ነኝ እርምጃሽ ግዞተኛ ላንቺ
ስለቀቅ የምሮጥ አስረሽኝ ስትፈቺ።
መኖርሺን እንጃ ስሜትሽ ሕልም ነው
የራቀው ሰማይ ነሽ የማይዳሰሰው።
የተረሳሽው ነሽ ያለፈው ትናንት
ማነው የሚያስብሽ እሌለሁበት?
ሽቱና ቅባትሽ የታለው መዓዛ?
የውሀ ሽታ ነው የተነሣው ለዛ።
ጌጥሽ ወዴት ይሆን ያለ ቅስቃሴ?
ገዳም የገባ ነው የሞተ መነኩሴ።

የምትጫወችው ሙዚቃው የታለ?
አፌና ምላሴ ድምጼም ዝም ካለ፡፡
እኔ ነኝ የሆንኩት ሳላውቀው አንቺን
ለኔ ብዬ ላንቺ ጤና ስለምን፡፡
በሓሳብ መሣሪያ የፈጠርኩሽ እኔ
ቦታም የሰጠሁሽ ፅድቅና ኩነኔ፡፡
በቅርፅ አሳምሬ በቀለም ቀብቼ
የእግዚአብሔርን ፀዳል ብርሃኑን ሰርቼ፤
የኔ ማየት መስማት መሆኑን ሳላውቀው
ሳላውቀው መሆኑን ሐሳቤ በሞላው
የሳምባዬ ወናፍ የልቤ ጭፈራ
የደሜ መሯሯጥ የጉበቴ ሥራ፤
አንጎሌ መንፈሴን እያውለበለበው
ትንፋሼ እሳቱን እያቀጣጠለው
ገላዬ ሲጫጫስ ሲቃጠል ሲፍም
ስበላ ሲሞቀኝ ስሮጥ ስደክም፤
የፍጥረት ግዴታ አካሌን ሲያሠራው
እየቆሰቆሰ ሕይወት ሲመግበው፤
አለሁ ብዬ ሳስብ አንቺ ነሽ ምክንያት
ማነሽ በኑሮዬ ቤት የሠራሽበት?
ምንድን ነሽ? ምንድን ነሽ? ምንድን ነሽ? ምንድን ነሽ?
ካንቺ ጋር እያለሁ ሳውቀው የማላውቅሽ
ቅመም ነሽ ዝንጅብል ቅርንፉድ ቀረፋ
የነጠረ አረቄ የእህል አረፋ?
የሚያንገዳግደኝ እግሬን ያሳሰረው
ምንድን ነው ጥንስሱ ለይቼ ልወቀው?
ወዴት ነው ቀበሌሽ መደበቂያሽ ዋሻው?
ከልቤ ውስጥ ይሆን የሚንደፋደፈው?
ወይም ባዶ ቦታ ዓይን የማይደርስበት
ጫጫታ ሁካታ ጩኸት የሌለበት?
እንቆቅልሽ ነፍሴ ንገሪኝ በርጋታ
ጨንቆኛል ጠቦኛል ያለሽበት ቦታ፡፡
ነፍሴ ተገለጪ መኖሬን ላስታውስ
የት እንደምትሔጂ?
የት እንደምትቀሪ?
ምን እንደምትፈቅጂ?
ምን እንደምትሠሪ?
ሲወሰድ ጀምሮ አብሮኝ የሚኖረው የሚንቀሳቀሰው
ይኸ ሰውነቴ ሲበተን ሲፈርስ፡፡

# አለርጅስ

እንግዳ ነበርኩኝ ሐርጌሳ ወርጄ
ምሳዬን ልበላ ወደ ሆቴል ሔጄ
በፀሓይ ከሥዬ ብለው ውሃ ስጠኝ
ባርያው ሒድ አለና እንግሊዙ ሸኘኝ።

# ስንኖር

ሁሉም ይለወጣል
ያለፈው ጨልሟል
ግልፅ ነው ዛሬ ቀን
መጭውን አናውቅም
አዲስ መንገድ አለ
ሰው ካዘነበለ
ወደ ስሜቱ ግብ ወደ ልቡ እርምጃ
ካየ፤ ካስተዋለ፤ ካሰበ፤ ከሔደ
መጥፎ ነው ያለውን ለምዶት ከወደደ
የሚፈልገውን አያጣውም እንጃ!
ምንድን ነው ብቻነት? እየኖሩ መጥፋት
ከሰው ማህል መውጣት
በሐሳብ ጎዳና መብረር መባከን
ለመያዝ መሞከር የማያዩትን
በኀዘን ምን አለ? ደስታስ ምንድነው
ሰመመን ትካዜ ምን መሠረት አለው?
ሳቅ፤ጨዋታ፤ ፍቅር፤ ምንድን ነው ዓይነቱ
ጥላቻና ቁጣ ወዴት ይሆን ቤቱ?
ይህ ሁሉ ሐሳብ ነው
ሐሳብ ግብ ይኑረው
ሔዶ ዞሮ ዞሮ ይመለስ ከቦታው
ይታይ መልኩ ይውጣ ይውረድ ክንብንቡ
ይናገር፥ ያስረዳ፥ ይገለጥ ጥበቡ
ሓሳብ ነው ሥራችን፤
ነው ሓሳብ ኑሯችን፤
አመል ጥብቆ ነው፤
ገላን የሚያለብሰው
የልጅነት አመል የልጅነት ልብስ፤
ሲያድጉ የሚቀር ነው የሚበጣጠስ።
አዲስ ልብስ ይሰፋል፤
አዲስ እድገት ሞልቷል።
ያልደረጀው ጊዜ ልጅ የሚኖርበት፤
ይሻራል፤ ይቀራል፤ ይረሳል ሲተውት።
የማኅበር ኑሮ
የዱሮውን ሽሮ
በሰፊው ይገልፃል፤ ብዙ ጓዝ ያመጣል፤
ማስተካከል ያሻል።
ከሚሮጠው ጋራ እርምጃን ማስገባት፤

ከሚቀመጠውም ሔዶ ቁጭ ማለት፡፡
　　መሳቅ፣ መተዋወቅ፣ መጫወት፣ መውደድ[1] ነው፣
　　ጊዜ እንዳቀረበው፡፡
ግዴታ ይመጣል፣
የማይፈልጉትን ጊዜ ያስለምዳል፡፡
　　በሕይወት ሰንሰለት ሁላችንም ታሥረን
　　ስንኖር ልዩ ነን፣ ስናስብ ብዙ ነን፣
　　ስንሠራ ግብ አለን፡፡
ያሻናል መሞከር፣
ማድረግ ወይ መናገር፡፡
　　ሙከራ ነው ሕይወት፣
　　ብዙ ሳንክ ያለበት
　　ትልቁ ዳገት ላይ ትልቁ ቁልቁለት
　　ነው የሚያንሸራትት፣
ያኛው ይለቀቃል ይኸው ሲጨበጥ፣
በዚህ ይረገጣል በዚያኛው ሲቧጠጥ፣
　　ሲሔዱ የሚታይ ኋላም የሚረዱት፣
　　የሚያስተካክሉት፣
አንደኛው ሲያስቸግር ሌላው ጠቀለለ፣
የሚገለፅ አለ፡፡
　　ይኸ ሲፈራርስ ያ ይመሠረታል፣
　　በዚያኛው ሲዘጋ በዚህ ይከፈታል፣
　　ሳይደክም የሮጠ ከግቡ ይደርሳል፡፡
አለመሰልቸት ነው ማስቀረት ፍርሐትን፣
አለመተው ግብን፡፡
　　ላቀዱት ዓላማ ፊትን ሳይመልሱ
　　መሥራት ነው መታገል ኃይል እስኪጨርሱ፡፡
መታገሥ፣ መሞከር፣ ማሳለፍ፣ መጠበቅ፣
ሲናደዱ መሳቅ፡፡
　　ዕድል ጉዞ ሲይዝ ሲጠፋ መከራ
　　የድካሙ ፍሬ ተለቅሞ የጠራ፣
　　ይሰጣል አዝመራ፡፡
ስለዚህ መሞከር መሞከር መድከም ነው፣
ስንኖር እንደሰው፡፡

---

[1] ጋዜጣው "መውድ" ነው የሚለው፡፡

# የዓለም መራራነት

*ያለም መራራነት ነው የሚጣፍጠን*
*መቾ መጣፈጧ፣*
*ኮሶውን በማሯ ጠቅልላ ስትሰጠን ስትሰጠን እሳቱን*
*አመድ አስመስላ ሽፍና ረመጡን፡፡*
*ስትሰጥ ማየ ሕይወት ስትሰጠን መዳኒኒት*
*መርዟን ጨምራበት፡፡*
*ስትሰጠን እሬቱን ስኳር አስመስላ*
*እንደ ጎመን ሠርታ ሳማዋን ስንበላ፡፡*
*እሷ ትዞራለች*
*ፀሐይ ትሞቃለች*
*እኛን በብርድ ላይ በጨለማ ጥላ፡፡*
*ያለም መራራነት*
*የሚያቀራምድ ነው፣ የሚያኮራምት፡፡*
*ስትወስድ ወደ ኋላ፣ ስትወስድ ወደሌላ*
*ምሥጢር ያላት መስላ፡፡*
*ከቤተሰብ ማህል*
*ሰው ስታስኮበልል፡፡*
*ስትወስድ ስጦታዋን*
*ለገፀበረከት ያቀረበችውን፡፡*
*ሌባ ናት ሰራቂ*
*ቀጣፊ ነጣቂ፡፡*
*አባባይ ቀልማዳ፣ አታላይ አስመሳይ*
*ዋሾ ናት ወላዋይ፡፡*
*ሰው ሊኖር ባለም ላይ መቾ ተፈጠረ!*
*መንገደኛ እንግዳ*
*መሽቶበት የመጣ*
*ሠራተኛ አገልጋይ ነው የተቸገረ፡፡*
*ብዙ ነው ልፋቱ*
*ሲፈጠር፥ ሲመጣ፥ ሲወጣ ከቤቱ፡፡*
*አይችልም መፅናናት*
*በደመ ነፍስ ባህርይ እንደተቀረፁት፡፡*
*እንዳህያ እንደጅብ ወይም እንደጦጣ*
*ወይም እንዳንበጣ*
*የማይቸገሩት ለምን ያስባሉ?*
*ከብቶች ይግጣሉ፣ ወፎች ይዘፍናሉ*
*አበቦች ያድጋሉ፡፡*
*ውስጡን አላወቁም፣ አልተመራመሩም*

ሲመጡ ወዳለም
የውሸት ሥዕል ናት
ለዛዋ እሚጠፋ፤ ቀለሟ እሚጠፋ
ሽታዋ እሚጠፋ።
ጠረኗ እሚያባርር፤ ጣሟ እሚከረክር
ቧልቷ የሚያስመርር።
የሰው ልጅ አንድ ባንድ ልታንሸራሸረው
ሁልጊዜ እንግዳ ነው።
ማናፈስ ማቅበጧ
ማቻኮል ማሮጧ ።
ያለም መራራነት ነው የሚጣፍጠን
መቾ መጣፈጧ!

# የባሕር ቅርድዶች

የሚሽቀዳደሙት የባሕር ቅርድዶች ወዳሸዋው መጡ
የፀሐዩን ጮራ ይዘው እየሮጡ፡፡
ይርመሰመሳሉ፤ ይረበረባሉ
ያብረቀርቃሉ፡፡
ምንድነው ጉዳዩ!
ነፍስ አስቆጥቶ የሚያሯሩጣቸው?
ተልከው ይሆናል አንድ ነገር ይዘው፡፡
ከባሕሩ ማህል ዓሣው ሲነጋገር
ወይም ከሩቅ ጠረፍ መርከብ ሲሽከረከር
ወይም ከጀልባው ሥር፡፡
ማዶ ከሚታየው ከትንሹ ደሴት
ከተንዘራፈጠው ከጋራው አቀበት፡፡
ይዘዋል በመላ፡፡
ማን ያውቃል ምን ይሆን?
ትርጉሙ ረቂቅ ነው የቋንቋቸው መጠን፡፡
እነሱም አያውቁት /ይቻላል ለማለት/
ምን እንዳስነሳቸው አጥመልምሎ ድንገት፡፡
ምን እንደሚሠሩ የት እንደሚሄዱ
የፀሐዩን ጮራ ሲያመጡ ሲወስዱ፡፡
አሸዋ ሲገፉ
ዓሣን ሺከሙ ሲጥሩ ሲለፉ፡፡
ዛጎል አንከባለው ወደዳር ሊያወጡ
ሲጋጩ ሲሮጡ፡፡
አንዱ ሌላ ሲሆን እያበጀ ቅርድድ
ያኛው በመከተል የሱን ቦታ ሲወስድ፡፡
ኑሮአቸው ነው ውሸት
ምሥጢራቸው ባዶ አልቦ ነው ቀለበት
ይኸ ሁሉ ድካም ከቶ ለምንድነው?
መሬት ለማቅናት ነው?
ባሕር ለማስፋት ነው?
አገር ለመያዝ ነው?
ልፋታቸው ከንቱ!
ግን ትርጉም ይሰጣል
ይኸ ነው እውነቱ
ሁኔታው ሲለወጥ የቅርድድነቱ፡፡
ተንደርድሮ መጥቶ ሲሔድ ወዳሸዋው
መሬቱ ሲውጠው፡፡
ወደተነሣበት ዳግም ሳይመለስ
ፈርሶ ሲበታተን ከጠረፉ ሲደርስ፡፡
ቅርድዱ የታለ?

የዱሮ ሁኔታው መልኩ ከተጣለ።
ያ ሁሉ መርመስመስ ያ ሁሉ ማብረቅረቅ
ያ ሁሉ መሯሯጥ ያ ሁሉ መፍለቀለቅ
ጠፍቶ ሲዘባረቅ።
መንቀሳቀሳቸው በኋላ ዝም ሲል
ከትንኝ አንስቶ ከቁንጫ ቅማል
ከዝሆን ከግመል።
በጣም አዋቂውን እንስሳ ከሁሉ፥
ሰውን ይመስላሉ።

# አንተ ነህ መስከረም

ማለቂያ በሌለው ደማቅ ሰማያዊ፤
ከሩቅ ያለው ጋራ ተነክሮ ሐምራዊ፡፡
በዚያ ላይ ደመናው እንደ ጥጥ ተነድፎ፤
እየተራራቀ ሲያንጃብብ ተቃቅፎ፡፡
አንተ ነህ መስከረም፤
የሐምሌን ጨለማ የነሐሴን ዝናም፤
የሻርከው አንተ ነህ፤
በብርሃን ውበትህ፡፡

በክረምቱ ወራት ሰማዩን ያስጌጠው፤
የማርያም መቀነት በቀለም ያበደው፡፡
ጤዛው አርሶታል መሬቱ ላይ ለቆ፤
በቀይና ብጫ መስኩ ተለቅልቆ፡፡
ወንዝና ጅረቱ ድንጋይና አፈሩ፤
አገሩ ውብ ሆኗል ሜዳው ሸንተረሩ፡፡

ዕንቁጣጣሽ አንተ ስጦታህ የበዛ፤
ለሰው መታሰቢያ ውበት የምትገዛ፡፡
በሽቱ መዓዛህ ለውጠው ዓመቱን፤
ይታደስ ያረጀው ፍጥረት ሌላ ይሁን፡፡
ከምረው ዘመኑን ካበው ባመት ባመት፤
በወሩ ደረጃ ፍጥረት ይጓዝበት፡፡
ፍየሎች ይዝለሉ ቅጠል ይበጥሱ፤
ከተሰደዱበት ወፎች ይመለሱ፡፡
ይልቀሙት እህሉን፤ ይሥሩ ቤታቸውን፤
ይስፈሩበት ዛፉን፤
የደስደስ ያሰሙ ንቦች ይራኮቱ፤
ይንጠራሩ አበቦች ይንቁ ይከፈቱ፡፡
አንበሳና ግልገል በመስኩ ይፈንጩ፤
ከብቶች ሣሩን ይንጩ፡፡
ሕፃናት ይሩጡ ይሳቁ ይንጫጩ፤
ዛፎች ይተንፍሱ፤ የነፋሱ ጠረን፤
ይሰራጭ በቦታው ያውደው አገሩን፡፡
ዓደይ አበባ ነህ የመስቀል ደመራ፤
ጠረንህ አልባብ ነው አየርህ የጠራ፡፡
ያገር ልብስ አንተ ነህ ነጭ እንደበረዶ፤
ሰው የሚያጌጥብህ ጥበብህን ወስዶ፡፡
ቡቃያ ነህ እሸት ጓሚያ የበሰለ፤
አረንጓዴ ልብስህ በጌጥ የተሳለ፡፡
ጥቁር አረንጓዴ፤ ብጫማ አረንጓዴ፤

ቀለም ! ቀለም ! ቀለም !
የሚስተካከልህ የሚያስንቅህ የለም፡፡
ኀዘን የምታርቅ የገነት ምሳሌ፡፡
ይታደል ወለላህ ጠጁ በብርሌ፡፡
ይስከር በደስታ ሕዝቡ ይሳሳቅ፤
ድምፁ እየተማታ ሙዚቃው ይፍለቅ፡፡
ዕንቁጣጣሽ ብለን እንስጥህ ሰላምታ፤
ይጨብጨብ ለዝናህ!
ይጨብጨብ ለሥራህ!
ይጨብጨብ ለመልክህ!
አንተ ነህ መስከረም፡፡
ዘመን የምታድስ አስጊጠህ በቀለም፡፡

# የሙዚቃ ድምፅ

የዛፉ ቅርንጫፍ የበገና ቅኝት
ነፋስ ሲያውተረትር የሚጫወትበት ፡፡

እዎጨበጨቡ ፤
ቅጠሎች በጃቸው ዜማውን ሲያደምቁ
ወፎች ድምጻቸውን እያስረቀረቁ ፤
ወንዙ እየተላጋ ፤
እየተጋረፈ ሲሔድ እንዳለንጋ ፤
ባሕር ሲገላበጥ
እየተንጠራራ ወደቡን ሲቧጥጥ ፤
መብረቅ ደመናውን ሰንጥቆ ሲወጣ
እያስገመገም ሰማዩ ሲቆጣ ፤
ሙዚቃ ተወልዷል ፡፡
ፍጥረት ተሰብስቦ መዝሙር ይዘምራል ፡፡
የቤቱን ቆርቆሮ
ዝናም ሲደበድብ አርጎታል ከበሮ ፡፡

ከሩቅ አገር አለ ደወል የሚመጣ
ከቤተ ክርስቲያን ተሰርቆ የወጣ ፤
ትንንሽ ደወሎች ፤
የሰዓት፤ የጥሪ፤ የተማሪ ቤቶች ፤
የቀጥቃጭ መዶሻ ብረት ሲያጠፈጥፍ ፤
ትልልቅ ፋብሪካ ጭሱ ሲያነፈንፍ፤
መኪና እየጮኸ ሲሔድ ሲተላለፍ ፤
ሁሉም ተሰብስቦ በቅደም ተከተል
ሙዚቃን ቀስቅሷል ፡፡
ሙዚቃ ተፈጥሯል ፡፡
አለ ትልቅ ጆሮ ፡፡
አለ ሌላ ጆሮ ፡፡
ይህን ሁሉ ጩኸት ሰብስቦ አስተባብሮ
የሚሰማው አለ ፡፡
የሚወደው አለ ፡፡
ከቅርብ አውራ ዶሮ ሰዓቱን ሲያስታውስ ፤
ድመቶች ሲጣሉ፤
አራዊት ሲአስካካ ከብቱ በመላቀስ፤
እንጨት ሲገነጠል ሣሩ ሲርመሰመስ ፡፡
ለሙዚቃ ስልቱ
ድምፅ ነው የሚያግዝ ተጨማሪ ምቱ ፡፡
ጥቃቅን ፍጥረቶች
ትሎች፤ ሸረሪቶች፤ ጉንዳኖች፤ ቁጫጮች፤

ማነው ያዳመጠ ሲጮሁ ሲዘፍኑ?
ሰውም ባይሰማቸው ፣
የሚያዳምጣቸው፣
አለ ልዩ ጆሮ ፣
አለ ሌላ ጆሮ ፣
ዜማቸውን ይዞ የሚዘምር አብሮ ።
የሙዚቃ ድምፅ
አለ ሁሉም ቦታ፣ አለ የትም ቦታ፣
በቅጠል ኮሽታ ፣
በወሀ ጠብታ ፣
በንጋት በሌሊት በብርሃን በማታ፣
ወይ ከባዶ ቦታ።
ሲወለድ ይመጣል የሙዚቃ ስሜት
ከሰማይ ከመሬት።
ይህን ሁሉ ጩኸት ።
አለ ትልቅ ጆሮ
አለ ሌላ ጆሮ
ለቅሞ እያከማቸ ሰብስቦ አስተባብሮ ፣
የሚሰማው አለ ።
የሚወደው አለ ።

# የፍቅር ሰላምታ

ጠጉርሽን ዳብሶ በጆሮሽ ያለፈው
ነፋሱ ምን አለሽ?
በመስኮት ላይ ሆነሽ፡፡
የፍቅሬን ሰላምታ ሲያስተጋቡ ይዘው
ተራሮች የላኩት፤
በሩቅ የሚታዩት[1]፡፡
የሚወዛወዙት ቆመው በመስኮትሽ
ዛፎቹ ምን አሉ?
ይንሾካሾካሉ፡፡
አይተዋል ደብዳቤ ማታ ስጽፍልሽ
ይግለጹ ምሥጢሩን፤
ልቤ መሸበሩን፡፡
ልብስሽን ስትለብሽ ወፎች የሚዘፍኑት
የሚሉት ምንድነው?
ጡቶችሽን አይተው፡፡
በፍቅርሽ ሰላምታ ልቤን እንዲያክሙት
ላኪያቸው ያምጡልኝ፤
መድኃኒቱን ይስጡኝ፡፡
ኮከቦች ከሰማይ ይጠቃቀሳሉ
ውበትሽን አይተው፤
በቅርጽሽ ተደንቀው፡፡
በሰማዩ ባሕር ጠልቀው ይዋኛሉ
ፍቅርሽን ሊይዙ
ወደኔ ሊጓዙ፡፡
ምን አለች ጨረቃ በመስኮትሽ ገብታ?
ስትነካ ፊትሽን፤
ተደግፋ አልጋሽን፡፡
ልኬልሽ ነበረ የፍቅር ሰላምታ
ጠይቂአት ውሰጂ፤
መልሱንም ስደጂ፡፡
የቤተ ክርስቲያን ደወሉ ዘመረ
ምን ሆኖ ይጮኻል?
ሰው ይሰበሰባል፡፡
ጉዳችንን አይቶ ገልጦ ተናገረ
እባክሽ ለፍቅር
ሞተን እንቀበር፡፡
ምነው ምን ፈለገ ሲጨፍር ከበሮ?
ተነሣ የሚለኝ?

---

[1] ጋዜጣው ላይ "የማታዩት" ነው የሚል፡፡ የኅትመት ስህተት ይሆናል በሚል ነው በድፍረት "ማ"ን ወደ "ሚ" የለወጥኩት፡፡

የሚቀሰቅሰኝ፡፡
ፍቅርሽና ፍቅሬን በመሐረም አስሮ
እንሒድ ተቃቅፈን፤
ደብቆ ይውሰደን፤
የበረረው ልቤ ካጠገቤ ጠፍቶ
ምን ምሥጢር አወራ?
ደንግጦ እየፈራ፡፡
ስታንጎራጉሪ መኝታሽ ቤት ገብቶ
የፍቅሬን ሰላምታ
ይስጥሽ በቀስታ፡፡

# የዓለም መጥፊያ

ደረሰ ይሉናል ዓለም ማለፊያዋ
ዋ!
የሰው ነገር ፤ ዋ !
ጊዜው መቸ ገና ፤
መቸ ደረሰና ።
ሰው ነው በገዛ እጁ የራሱ መፍረሻ፤
ሌላ ነገር ሲሻ፤
አይበቃኝም ብሎ ሲሰስት[1] ሲሻማ
የሌሎቹን ዓለም ሲናጠቅ ሲቀማ፤
ይፈጥራል ጦርነት፤
ይጠዛጠዛሉ ዓለማት ካለማት።
ከኮከብ ጨረቃ ከጨረቃ መሬት፤
ያቶሚኩ ርችት ፤
ይላካል ፤
ይመጣል።
የከዋክብት መስመር ጉዞአቸው ይናጋል።
ተጋጭቶ እየሄደ አንዱ ክበብ ካንዱ ፤
ዓለሞች ሲወርዱ ፤
ዓለሞች ሲፈርሱ ዓለሞች ሲናዱ ።
እልፊት የሚመጣው ፤
ወዮ !
ያን ጊዜ ነው ።

[1] ጋዜጣው ላይ የታተመው "ሲስሰት" ነው የሚለው።

# ይራመዳል ገና !

ወዴት አለ እንቅፋት !
ለዚህ ትንሽ ተባይ ፤
መሬትን አስጊጦ ላደረጋት ገነት።
ባራት እግሩ ሲሔድ ባለም ላይ ገንፍሎ
ሲንፏቀቅ ሲጎተት ኋላም ብድግ ብሎ ፤
አንጎሉ ረቀቀ።
ማድረግ መፍጠር ቻለ እየተናነቀ።
በሥራው አደገ ፤ በአእምሮው አደገ፤
በሐሳቡ አደገ።
ዘልቆ እየጠለቀ በመመራመሩ ፤
ለውጥ እየፈለገ በመከራከሩ ፤
ሁሉንም በለጠ ።
ሁሉንም ጨበጠ ።
የጥበብ ዕንቁላል አስኳሉ ፈረጠ
ቅርፍቱ ተሰብሮ ዛፉ ተመጠጠ ።
የባሕር ሆድ ዕቃው ወጣ ተበዝብዞ ፤
ሰማይ ተሰንጥቆ ፤
ዕውቀት ይለቀማል በብልሃት ተይዞ።
የመሬት የውስጡ የሥር የማህሉ
አካባቢው ሁሉ ፤
ተጠና ታወቀ ኃይል እየተስፋፋ
ጉልበት ተከማቸ መሰናክል ጠፋ ።
አቶም ተነቆረ !
አየር መጋረጃው በሰው ተበገረ ።
መች እንዲህ ሆነና
ይራመዳል ገና።
ከተማውን ሠርቶ ይኖራል በሰማይ
ባዶ ቦታ ሔዶ ይዘረጋል ድልድይ ።
የስልኩ ማዞሪያ " አሎ ጨረቃ " ነው
ቁርሱ ከማርስ ላይ ከቬነስ ላይ ምሳው ፤
ከመሬት እራቱን ፤
በልቶ ይጨፍራል ሜርኩሪ ላይ ዳንሱን ።
የብርሃንን ፍጥነት ሲሽቀዳደም ይዞ
ከመ ቅጽበተ ዓይን ይሔዳል ተጉዞ ።
ያንዱ ኮከብ መቅናት ለሌላው መረጃ
ሆኖ መራመጃ ፤
ዓየርን ይተዋል ሲፋጠን ወደላይ
ዓለማት ተገዝተው ይጠበዋል ሰማይ ።
ሁሉን ይለውጣል ።
ለማየት ለመስማት ፤ ለማሽተት ለመንካት፤

ለጣም አዲስ ዓይነት ፤
ሥያሜ መጠሪያ መንገድ ይሰጠዋል ።
ባዶ ቦታ ሆኖ ፈጥሮ መገናኛ
በሴኮንድ መቶኛ ፤
ሁሉንም ይሠራል ።
የጥበብ ምዕራፍ አዳዲስ ይሆናል ።
ከሌላው ዓለም ላይ መከላከያውን
ፈጥኖ ይጋፈጣል ።
የፀሐይን ፀሐይ ፤ የፀሐይን ፀሐይ፤
ይኸ ትንሽ ተባይ !
በሥልጣኑ ገዝቶ ያስገብራቸዋል ።
መሬት ስታበራ ከጨረቃ ዛፍ ሥር
ይፈጥራል ሙዚቃ ቅኔ ሲደረድር ።
ያገኛል መድኃኒት
ሲኖር በከዋክብት ።
ሞትን ያሸንፋል !
ሁሉን ሲቆጣጠር . . . ይሆናል ።
ወዴት አለ እንቅፋት !
የት አለና ዳገት !
ለዚህ ትንሽ ተባይ ።
ገና ይራመዳል ።

ከጀርመን አገር

የሚያጽናኑ

ጅምር ሥራ፤

በየጊዜው የሚያድግ፤

ቀን የሚገፋ፤

ትንሽ ክፍል፤

ከዓለም ጣጣ የምትከልል፤

ትንሽ ወንበር፤

የምታቅፍ፤

የምትደግፍ፤

አሮጌ ልብስ፤

አብሮ ያረጀ፤

የነተበ።

አሮጌ ጫማ፤

ያገለገለ፤

የለፋ።

ማንቆርቆሪያ፥ ሣህን፥ ውሀ፤

ውሀ መታጠቢያ፤

ፎጣ– የሚሻክር፤

ምድጃ፤ ከሰል፤ እሳት፤

እሳት፤ ሙቀት፤

ቁራሽ ዳቦ፤

ወተት በጠርሙስ፤

ፍሬ በሣህን፤

ሲጃራ፤

የተጋመሰ፤

የሚጨስ፤

የጎረቤት ሙዚቃ፤

ከሩቅ የሚመጣ፤

ደብዳቤ፤

ማስታወሻ ደብተር፤

ጋዜጣ

የዘመድ ፎተግራፍ፤

የወዳጅ፤

የራስጌ መብራት፣

የግድግዳ ጥላ፣

የተሰቀለ ሥዕል፣

መጻሕፍት፣

መጻሕፍት፣

መጻሕፍት

መጠጊያ፣ መሸሸጊያ፣ መደበቂያ፣

የሚያጫውቱ፣

የሚያስተምሩ፣

የሚያነጋግሩ፣

አልጋ፣ ፍራሽ፣ ትራስ፣

የሚውጥ አልጋ፣

የሚያሳርፍ፣

ዕንቅልፍ፣

ዕንቅልፍ፣

ዕንቅልፍ፣

እንዲሁም ሌላ፤

እንዲሁም ብዙ፤

ብዙም ሌላ...

ያጽናናሉ።

# ዓፅም

ማነህ የተኛኸው?
እንቅልፍ የደበተህ ሥጋህን ጥለኸው።
ምን ኖረኻል አንተ
ንጉሥ ኖረህል ወይ፣ ኖረሃል ወይ ጌታ?
ወይ ቁርንጮ ለባሽ ለማኙ ከርታታ?
ሚኒስትር ደጃዝማች ወይም ፊታውራሪ
ባለብዙ ገንዘብ አሽከር አሳዳሪ
ኖረኻል ወይ አንተ?
አጥንትህ ወላልቆ እንዲህ የሻገተ!
ሥራህ ምን ነበረ? ቤትህ የት ነበረ?
እርስትህ የት ቀረ?
የተመራመረ አዋቂ ፈላስፋ
ብዙ መሰናክል ካለም ላይ የገፋ
ሳትሆን አልቀረህም፣
ጉድ ነው! መልክህ የለም።
ማነሽ ማነህ አንተ?
ማናችሁ እናንተ?
ማነሽ በዘመንሽ የውበት እመቤት
ሆነሽ የገዛሽው የወንዶችን ጉልበት?
በክንድሽ ያለቀው
ወጣቱ ጎልማሳ የት ነው የወደቀው?
ምን ኖረሻል አንቺ አጥንትሽ ይናገር?
እንጨት ተሸካሚ
ወይ ኩበት ለቃሚ
ወይ ልብስሽ ያደፈው ጥሬዋ ባላገር፣
ወይም ሽቅርቅሯ እስቲ ተናገሪ?
ሽቱሽ የጎረፈው መንጭቶ ከፓሪ
በወርቅና ባልማዝ በሉል እንደ ሆነ
ተጫውተሽ የሔድሽው ዝናሽ የገነነ።
እስቲ ተናገሪ ቋሚ ያዳምጣል
አንቺ ለመሆንሽ ምስክርሽ የታል?
ያሻኻል ምስክር
ሞተህ ስትቀበር
ድንጋይ ላይ ተፅፎ የሚናገርልህ
ምልክት የሚሰጥ አንተ ለመሆንህ፣
ሐውልት የሚያቆይህ
ዘመድ ያስፈልጋል ከሌላው ለይቶ
መንገደኛ እንዲያውቅህ ቆሞ ተመልክቶ።

"እገሌ ነው" ብሎ ታሪክ የሚያወራ
እንዲደነቅልህ ቀሪው ያንተ ሥራ
ተነሥ አንተው ጥራ!
እጎንህ ከተኙት ዓፅሞች በጉድጓድ
አለ ወይ ዘመድህ የምታውቀው ጓድ?
ወዴት ነው አባባ የታለች እማዬ
ጋሼ ወዴት ይሆን የት ቀረች እትዬ?
ጠፍቷል ምልክቱ
አጥንትና ሥጋህ ሲሰነባበቱ፡፡
ከሙታን ማኅበር በመዝገብ ገብተሃል
ማንኛውም አጥንት አስከሬን ሆነኀል፡፡
የሞት ጠባሳ ነህ አስታዋሽ ሥራውን
ከንቱ ነው የምትል አወይ ፍጡር መሆን!
የተንቀረፈፈው እጅ እግሩ ሸምበቆ
የተከፋፈለው ሰረሰሩ ለቆ፣
ጥርሱ ያገጠጠ ዓይኑ የወለቀ
ጎድኑ ተቆጥሮ ጅማቱ ያለቀ፣
የተገጣጠመ የተሠራ ባጥንት
ሥጋ ወዝ የሌለህ የሰው ዘር ምልክት፣
ሆነህ የተኛኸው
የማትታወቀው፣
ምን ኖረኻል አንተ?

# ይኸ ጊዜ

ሀቻምና በረረ፤
አምናም ተሻገረ፤
ዘንድሮም ይሮጣል፤
ሕፃን እያደገ ልጅ ይጎለምሳል።
ይጠፋል አሮጌው ወጣት እያረጀ፤
ጊዜ እየደረጀ።
ተከማችቶ አይሞላም፤
እንደምን በረረ፤ ይገርማል! አይቆምም።
መስከረም ሲቀባ ቀለም ባመት ባመት፤
አልተወም ማደሱን ያረጀውን ፍጥረት
ያደፈውን መሬት፤
ክረምትም ሲገባ ማጠቡን በውሀ፤
በተራው ሲተካ በጋም ከበረሃ፤
አልተወም ይለፋል፤
ሁሉም ይንፏቀቃል፤
ገመዱን ሲጎትት ጊዜ ይቀልዳል።
ምን ይሆን ይኸ ጊዜ?
የሰዓት እጆቹ ድምፁ ውዝዋዜ።
ወይም የሰው ዕድሜ ሰብዓና ሰማኒያ፤
ያመት መለወጫ የዘመኑ ጣቢያ።
ወይ ቀንና ሌሊት፤
ወይ መወለድ መሞት፤
ወይም ያለም መዞር የፀሐይ መታየት፤
ሙሉዋ ጨረቃ፤ የጨረቃ መጥፋት።
ጊዜ ይኸ ይሆን?
ሰው ነው የሚሔደው ጊዜን እየለካ?
ወይስ ጊዜ ቆሟል ምንም ሳይነካ?
ምናልባትም ደግሞ አብረው ይሔዳሉ፤
እየተቻኮሉ፤
ወደኋላው ሲቀር ፍጥረት በድካሙ፤
ጊዜ ይራመዳል ሲቃለል ሸክሙ።
ባንድ በኩል ደግሞ ጊዜ ፍፁም የለም፤
መነሻ መድረሻ መካከል የለውም።
ሰው ነው የሚለካው፤
ፀጥታን ሰንጥቆ ድምፅ እንደሚወጣው።
ጨለማን ሲረታ፤
ብርሃን እንደሚገኝ በጠቀረው ቦታ።
ሰው በጊዜ ላይ፤
ይሆናል መስታዎት መኖሩን የሚያሳይ።
እንዳይሆን ያስፈራል!

ይኸም እንዳይባል፣
ሰው ቢኖር ባይኖርም መሬት መሽከርከሯን፣
ወር እየቆጠረች ጨረቃም መውጣቷን፣
ባህር መላወሱን፥ ዝናም መርከፍከፉን፣
አፈር መንፏቀቁን፣
አይተውም ሥራውን ምንም አያቋርጥ
ሰው ነው ተመልካቹ በዘመን ላይ ሲሮጥ::
<u>ውሸት ነው ይጠፋል!</u>
ጊዜም እንደሌላው፣
ጊዜም ከሚወደው፣
ጊዜም ከጊዜው ጋር ሞቶ ይቀበራል::

* * *

የነቢያት ጊዜ ዛሬ ወዴት አለ?
የነቄሳር ጊዜ ዛሬ ወዴት አለ?
ጄንጂስካን ግዛቱ፣
የሂትለር ኩራቱ፣
<u>ዛሬ ወዴት አለ?</u>
ቅኝ አገር መሻማት ዛሬ ወዴት አለ?
የመርከብ ወንበዶች ጊዜአቸው የታለ?
እንደ ዱሮ አይሆንም
ታሪኩ ቢወራ ሐተታው ቢለቀም፣
እንደ ጥንቱ አይሆንም::
መሰሉም ቢመጣ ጥቂት ተለውጦ፣
ያለፈውን ጊዜ ጭራውን ቆንጥጦ::

"ታሪክ ተደገመ"
ይባላል ሲጠፋ ጊዜ እየታመመ
በራሱ ከረጢት ገብቶ ተጠቅልሎ፣
ለብቻው ሲደበቅ ሸሽቶ ተገልሎ፣
አስታዋሽ ሲያገኘው፣
እየታየ ጥላው::
ሁሉም ይለወጣል ጊዜ እየቆጠረ
አንዳንዴም ይረሳል እየተሰወረ
ጨረቃ እንደክብሪት ፀሐይ እንደሻማ
በርተው ይጠፋሉ፣
ተቃጥለው ያልቃሉ::
ሰማይ ተቀዳዶ እንዳሮጌ ሸማ
ከዋክብት አንድ ባንድ ወድቀው ተንጠባጥበው
የባህርይ ፍጥረቶች እንዳልነበር ሆነው
ሲመጣ ጊዜአቸው ፣
ያልፋሉ ጨልመው::

**የማያልፍ ምን አለ?**
**የማይቀር ምን አለ?**
**ሞትም ሙት ይሆናል የሚሞት ሲጠፋ፤**
**ጊዜም እየገፋ**
**የሚገፋው ሲያጣ ይሆናል የጠፋ።**

# የፍቅር ቃጠሎ

ጉንጭሽ ፅጌረዳ

ሞቆት የፈነዳ

ዓይንሽ የጧት ጨረር የበራ ማለዳ፤

የማትጠገቢ ጣፋጭ ከረሜላ የማር እሸት ነሽ

ጠብ አትይ አንጀቴ ባኝክ ብመጥሽ፡፡

ቆንጆ ነሽ አንቺዬ!

እሳተ ነበልባል ነሽ ነዳጅ ባካላቴ

ሆነሻል ሙቀቴ

ሆነሻል ሕይወቴ፡፡

የጋለው ትንፋሽሽ

የፈመው ምላስሽ

ማርኮኝ በከንፈርሽ፡፡

እጄን ሰጥቻለሁ

እስረኛ ሆኛለሁ፤

ያንቀጠቅጠኛል ወባው ቅናት ገብቶ

ልቤን አስፈራርቶ

ትኩሳት አምጥቶ፤

ፍቅርሽ አቃጠለኝ በመልክሽ ስተክዝ

ንከሽኝ ልደንዝዝ

እቀፊኝ ልቀዝቅዝ፡፡

# ሰው ሲሸነፍ

ማሸነፍ ምንድን ነው?
      የምኞት አዝመራ
የደስታ መከር፣
      የታጨደ ጣጣ
የተወቃ ችግር፣
      የሞተ መከራ፣
የሚነድ እሳት ነው ተዳፍኖ የበራ::
እያደር ጠፊ ነው፣
እያደር ቀሪ ነው ሲቆይ ይሰለቻል፣
      ዋጋው ይቀንሳል::
ሁልጊዜ በማግኘት፣
ዘወትር በማሸነፍ ዘወትር በመመከት፣
      በመግዛት በመቅጣት፣
ደስታ አይገኝም::
ሌላ ይፈልጋል የሰው ልብ አይጠግብም::
ለጥቅሙ የሚያስብ የተስገበገበ፣
መንገዱን የማያቅ ግቡ የጠበበ፣
      ስስታም ይሆናል
ለፍቶ ጥሮ ግሮ ሲያጋጥመው ዕድል::
ዕረፍት አያገኝም፣
ሲያስብ፥ ሲያጠነጥን፣ ሲታትር፣ ሲደክም፣
አንዱን በመጨረስ ወጥኖ ሌላውን፣
ያንን በመሰልቸት ሲጀምር አዲሱን፣
ያቅበዘብዘዋል፣
      ትዕግሥት ይነሳዋል::
ትንሽ መሰናክል እሾህ መንገዱ ላይ፣
የኑሮው ሕመም ነው የሕይወቱ ሥቃይ፣
ያገባዋል እልክ ደሙን አስቆጥቶ፣
ንዴቱን አምጥቶ
ይተዋል ይሉኝታን ከግቡ ለመድረስ፣
ወዲያ ወዲህ ብሎ ኃይሉን እስኪጨርስ
በመሸነፍም ነው፣
ሰው ደስታ ያለው::
      በመተው በመርሳት፣
በመልቀቅ በማጣት፣
      በመሸሽ በመፍራት::
ወደፊት ከመሔድ አውቆ በማፈግፈግ፣
ከማሰብ ለብዙ ጥቂት በመፈለግ፣
በማነስ ከማደግ::

በመጣል ከማንሳት፥ በመስጠት ከመውሰድ፤
በማልቀስ ከመሳቅ፤ በመቅረት ከመሔድ፤
ከመውጣት በመውረድ፡፡
ከመልበስ መታረዝ፤
ከማምለጥ በመያዝ፡፡
ክብርን ለመጠበቅ ደፍሮ ከመናገር
አንገት በማቀርቀር፡፡
በመዋረድና በችግር ተጎድቶ፤
በመውደቅ ተገፍቶ፤ በመናቅ ተጠልቶ፤
በኀዘን፤ በድካም፤ በሕመም፤ ባርምሞ
አግኝቶ በመክሰር፤ በመሻር ተሹሞ
ያውቃል ማ መሆኑን፤
ይረዳል አቅሙን፡፡
የሕይወት ለውጥ ነው ያለ በኑሮ ላይ፤
እንደ ቀን፤ እንደ ሌት ፤ እንደመሬት ሰማይ፤
እንደ ውሀ እንደሳት እንደልቅሶ ሳቅ፤
እንደርጥብ ደረቅ፤
ሁሉም ተለውጦ አንፃሩን ይይዛል፤
የሚሮጠው ጊዜ ጥቂት ይታገሣል ፡፡
ሰዓቱ ይቆማል፤
ደቂቃው ይተኛል፡፡
ይሸፈናል ወሩ፤
ይታሠራል ቀኑ፤
ቀስ ይላል ዘመኑ፡፡
የሚፈጥነው ሐሳብ ከጉዞው ሲመለስ፤
ያንዣብባል መንፈስ፤
የምትራወጠው ትቀመጣለች ነፍስ፡፡
አጥንትና ጡንቻ፤
ጅማትና ሥጋ፤
ዝለው ይወድቃሉ፤
ሰላም ያገኛሉ፡፡
ዕረፍትና ድካም ያሳዩታል ቤቱን፤
ይተኛል ዕንቅልፉን፤
ሲያውቀው መሸነፉን፡፡

# ሰው ፤ ግሩም ሰው !

ሰው ፤ ግሩም ሰው አንተ !
ለመጀመሪያ ነው ፤
የሰው ልጅ በሕይወት ጥሎ የተለየ
መሬትን ከውጭ እየዞረ ያየ
የስፑትኒክ በራሪ ፤
በሰማይ በራሪ በብረት በራሪ
ምንም ይሁን ማንም
ስም ዋጋ የለውም ::
አንደኛው ምዕራፍ ይኸው ተከፈተ ፤
ሰው ሰማይ ዳበሰ
ሰው ዓለምን ጥሎ ሔደ ተመለሰ
ሕልም እውነት ይሆናል
ሰው ይክበር ይመስገን የሰው ልጅ ይሞገስ
ለሰው መዝሙር ይውጣ ለሰው ልጅ ይደገስ ፤
ጎረቤቶቻችን ፤ በሌላው ዓለማት ውሸት ነው አይኖሩም ፤
ከረቀቀው ባሕርይ ከሰው ልጅ አእምሮ
በልጠው የሚገኙ በጥበብ በኑሮ
እርግጥ ቢሆን ኑሮ
( እስከ ዛሬ ድረስ ከሰው ልጅ ቢበልጡ )
ይችሉ ነበረ ጨረቃን ሊረግጡ
ይችሉ ነበረ መሬትን ሊረግጡ
ወደኛ ሊመጡ እኛን ሊጨብጡ
እልክ ነው ፤ ወኔ ነው ፤
የሰው ልጅ ኩራት ነው ፤
የሰው ልጅ ዕድገት ነው ፤
ጥበብ ጉድ ነገር ናት
ውበት ጉድ ነገር ናት
ሰው የሚደነቅ ነው !
የዘመን ላይ ጤዛ የመሬት እንጉዳይ
የጊዜ አዋራ የማያርፈው ተባይ
ሰው ውበት
ሰው ጥበብ ፤
ሰው ፤ ግሩም ሰው አንተ !
ይቅናህ በመንገድህ
የሰው ልጅ ምንጊዜም ጥበብ አይለይህ ፤
እንግዲህ ከዋክብት
እመኑ ገብሩ
ላዲሱ እንግዳ ሰማያት ዘምሩ
ሒድ የሰው ልጅ ድረስ
ዓለማትን አይተህ ከመሬት ተመለስ ፤
ይቅናህ በመንገድህ

# ፍቅር ጥላ ሲጥል[1]

በገና
ቢቃኙ ፤
ሽክላ
ቢያዘፍኑ
ክራር
ቢጫወቱ ፤
ለሚወዱት
ምነው
ሙዚቃ
ቢመቱ ፤
ቢቀኙ
ቢያዜሙ ፤
ቃል
ቢደረድሩ ፤
ጌጥ
ውበት
ቢፈጥሩ ፤
ቤት
ንብረት
ቢሠሩ ፤
አበባ
ቢልኩ ፤
ምነው
ቢናፍቁ !
አገር
ቢያቋርጡ
ቢሔዱ
ቢርቁ ፤
ዓመት
ቢጠብቁ
ዘመን
ቢጠብቁ ፡፡
ለሚወዱት ምነው....

---

[1] ጋዜጣው ላይ **"ፍቅርጥላሲጥል"** ነው የሚል፡፡ ጋዜጣው ላይ በዚህ መልክ የተፃፈው በቦታ ጥበት ምክንያት ስለመሰለኝ ብቻ ነው ያስተካከልኩት፡፡ ምን ማለቴ እንደሆነ ለመመልከት የሚሹ አንባብያን ጋዜጣውን እንዲመለከቱ እጋብዛለሁ፡፡

# ለ አ ባ ቴ[1]

እንቅልፍህን ተኛ
የዘላለም እንቅልፍ . . . . .
እንዳይቀሰቅሱ – ህ ፡፡
የዚህ ዓለም ፀሐይ የሚያጭበረብረው
ዓይንህን አይንካው፡፡ የዚያን ዓለም ስቃይ
የዚያን ዓለም እንቅልፍ የሚያባንነውን
እርሳው የኔ አባባ ፡፡
ጩኸቱን አትስማ ፡፡ ከበሮ ጸናጽል ፣
ፍታቱን ልቅሶውን ፣
ደረት ሲጠፈጠፍ ጠጉር መነጪቱን
አፈሩ ሲካበድ የድንጋዩን ጭነት
ግባ ተመሬቱን ፣
እርሳው አባባዬ ፡፡
አታስብ ይበቃል !
ዱሮም አንተ እንደዚህ ብዙ ጊዜ አይተሀል ፡፡
አንተም አባት ሞቶህ፣
አንተም እናት ሞታህ ፣
ወንድም እህት ጠፍቶህ ፣
ሚስት የልጆች እናት . . . . .
እንባህን ጠርገሀል ፡፡
ታውቃለህ ብዙ ነው ፣ መንገዱ ብዙ ነው፡፡
ሞት እንደንቆቅልሽ ፣
ጅምሩ ማለቂያው ፣
መካከሉ ዳር ነው፡፡
ታውቃለህ ሰው ኢምንት ፣
ሰው ጥቃቅን ነገር ፣
ሲኖር የማይታይ፣
በሚሊዮን እጥፍ ፣
በሚሊዮን ጊዜ በጣም ካላነሉት ፡፡
(ታውቃለህ የኔ አባት አስተምረኸኛል)
በመኖር በመሞት ፣
ልዩነት የሌለው ፣
ቢኖርም ልዩነት ፣
ከነፋስ ከውሀ መልኩ የቀጠነ
ዓይን የማይጨብጠው ፣

---

[1] የጋዜጣ ቦታ ለማብቃቃት ሲባል አንዳንዱ ስንኝ ተጨናንቆ የታተመ ይመስለኛል፡፡ ኦርጅናሌውን ፈልጎ ለማስተካከል መሞከር ያስፈልጋል፡፡

***ሕይወትን ሲያነቡት ወደ ግራ ሞት ነው ።***
***(ብለህ ነግረኸኛል ።)***
***ስለዚህ ግድየለም ።***
***እንቅልፍህን ተኛ ።***
***በጸጥታ ቦታ ካሳብ አልፎ ተርፎ ሐሳብ***
***ይኖር ይሆን ?***
***ግድ የለም !***
***ግድ የለም !***
***መመርመር አትሞክር ።***
***አንተው ሁን ፀጥታ !***
***ሕይወት የዘራውን የጤና ቡቃያ***
***በበሽታ አመዳይ ሞት እንደሚያጠፋው***
***በወዲያኛው ዓለም የፀጥታን ክዳን***
***ቢኖር ልዩ ነገር የሚቀሰቅሰው***
***አትንቃ ከንቅልፍህ !***
***በመብረቅ ነጎድጓድ ዓለም ይደባለቅ***
***ሰማይ መጋረጃው ይተርተር ይሰንጠቅ***
***ፀሐየ ፀሐያት ኮከብ ይንጠባጠብ ፤***
***ጨለማም ይጨልም ዓይን አውቆ እስኪጠፉ ፤***
***መሬት ጭቃ አዛባ እንደ ሊጥ ትበጥበጥ***
***ሌዋታን[1] ይንቀጥቀጥ !***
***ብሔሞት[2] ይንቀጥቀጥ !***
***ሳጥናኤል ይቆጣ ሲኦል[3] አፉን ይክፈት***
***እልፍ ዓለም ይቃጠል በገሀነመ ሳት ፤***
***መንግሥተ ሰማያት ባልማዝ ሉል ታብረቅርቅ ፤***
***ገነት ትፍካ ትሳቅ !***
***ጉዳይህ እንዳይሆን !***
***ዱሮ በልጅነት . . . . በጎልማስነቴ . . .***
***አደንቅህ ነበረ ።***
***ያ ድምፅ የውቀት ደወል !***
***የሃይማኖት ዜማ የሕይወት ሙዚቃ***
***ኃያል ግርማ ሞገስ !***

---

[1] "ሌዋታን፤... የባሕር አውሬ እንስሳ ፤ ዘንዶ ፥ ታላቅ ዓሣ ፤ ማናቸውም፡፡ እንስት ዐንበሪ ምድርን እነደ ዝናር እነደ ጋን ሰንበር ፥ ወይም እነደ ቀለበት እንዳንባር ዙራ ተጠምጥማ ዐቅፋ የያዘች የብሄሞት ዘውግ ፥ ጣምራው ኹለተኛው ፤ ዘሩ ለወየ ነው ፤ ሌዋ ዐቃፊ ተጠምጣሚ ፤ ታን ዘንዶ ፥ ወይም ወርድና ቁመት ግዘፈ ምድር፡፡ በተገናኘ የምድር መታጠቂያ ቅናት መቀነት ማለት ነው፡፡..." (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፥ 1948፥ ገፅ 561)፡፡

[2] "ብሄሞት፤ በቁሙ ፤ የየብስ ዐንበሪ ከባሕር ተፈጥሮ በየብስ የሚኖር ፤ ግሩማን አራዊት የሚፈሩትና የሚገዙት ከአራዊት ኹሉ የሚበልጥ መጨረሻ ግዙፍ ፥ የእንስሳት ራስ የአራዊት ንጉሥ ፤ በኩራቸው ቀዳማያቸው ፤ በተፈጥሮ የሌዋታን ወንድም ባሏ መሰሏ ። ... ባለብሉዮች ግን ዙኖን ይሉታል ። " (ኪዳነ ወልድ ክፍሌ፥ 1948፥ ገፅ 257)፡፡

[3] ጋዜጣው "ሶኦል" ነው የሚለው፡፡ ግጥሙ ፍች ሊኖረው የሚችለው "ሲኢል" በሚል ከተስተካከለ ብቻ ነው፡፡ የትየባው ስህተት የደረሰው "ሳኦል" ለማለት ሲሞከር ነው እንዳይባል ደግሞ " ሳኦል ፤ የሰው ስም ፤ በእስራኤል ላይ መዠመሪያ የነገሠ ንጉሥ" መሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ይታወቃል፤ ደስታ ተክለ ወልድም በጥቅሱ ውስጥ ይህንኑ ነው የገለፁት (**ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት**፥ 1962፥ ገፅ 1154)፡፡

ያ በሰው ልጅ አምሳል የተጎናፀፍከው ፡፡
ያ መመራመርህ ፤
    አስተዋይነትህ፡፡
አደንቅህ ነበረ !
ዱሮ በንግግር ፤ ዱሮ በትምህርት
ጥበብ ዕውቀት ሆነህ ፤
    ፀሐይ ብርሃን ሆነህ ፡፡
አሁን ጊዜው ሲመሽ . . . . .
የድሜ ሳት ተቃጥሎ ከሰል ሲሆን ሕይወት
    አሁን በዝምታህ ፤
አሁንም አያለሁ ፤
አያለሁ በፊትህ ዓይኔ በንባርሶ
የውበት ፈገግታህ አልጠፋም ጨርሶ ፡፡
ትዝታህ አልጠፋም
    ደግነትህ አለ ፡፡
ዕውነቱ ክርስቲያን ዕውነቱ ሳምራዊ
ያ ቅዱስ ትህትናህ ፤ ቅዱስ ሰማያዊ ፡፡
ድካምክን አውቃለሁ ፡፡ . .
ድካምህ ልፋትህ ፤ ላገር ለወገንህ ፤
ለሕግ ለነፃነት !
    ለምነትህ ለውነትህ !
ሳቅ አሁንም በሞት ፤
    /እዚህ የሌለ ሳቅ/
በፀጥታው ቦታ ሙዚቃ ሁንበት ፤
    /ዝም ያለ ሙዚቃ/
እረፍት አድርግ አሁን ፡፡

# እኔ እወድሻለሁ

ብዙ ሺህ ዘመናት
　　እልፍ አዕላፍ ሌሊት ፤
ሚሊዮን መሰለኝ
ፍቅሬ አንቺን ስወድሽ ቀኑ ረዘመብኝ ።
　　እኔ ወድሻለሁ
የሰማይ መሬቱን ፤
የባሕር ስፋቱን
እንዳለም ዳርቻ የርቀቱን ያህል ።
　　እንደ ጽጌረዳ
　　እንዳደይ አበባ ፤
　　እንደ ሎሚ ሽታ ፤
እንደ ከርቤ ብርጉድ ፤ እንደጣን ጭስ እንጨት
ውድ እወድሻለሁ
አበባ እንዳየ ንብ ፤
እንደ ቢራቢሮ ጫካ እንደ ሚያስሰው
ፍቅርሽን በፍቅሬ በፍቅርሽ ልቅመሰው ።
ማር ወለላዬ ነሽ ከረሜላ ስኳር
አማርኛ አይበቃ
　　(ወይ ጉድ ! )
ባለም ቋንቋ ሁሉ ቢወራ ቢነገር ።
　　እኔ እወድሻለሁ ።
እንደ ማታ ጀንበር ፤
እንደ ጨረቃ ጌጥ ፤
እንደ ተወርዋሪ ኮከብ የማልጠግብሽ
ስወድሽ ፤ ስወድሽ ፤
　　ስወድሽ ፤ ስወድሽ ።
ጡት እንዳየ ሕፃን ወተት እንዳማረው
ጠጋ በይ ዘመዴ አፍሽ ሕይወቴ ነው ።
ጣይ ላይ ያለ ቅቤ[1] . . . . . . . .
ገላዬ ገላሽን ሲነካ የሚያልቀው
አፈር መሬት ትቢያ ውሀ እንደሚበላው
ፍቅሬ አንቺን ስወድሽ. . . . . . . . . . . .
　　ብዙ ሺህ ዘመናት
　　እልፍ አእላፍ ሌሊት ፤
ውድ እወድሻለሁ ።
ዓይኖችሽን ባይኔ ተዳክሜ እያየሁ ።
ስወድሽ ፤ ስወድሽ ፤
　　ውድ እወድሻለሁ ።

---

[1] ጋዜጣው ላይ "ያለቅቤ" ተብሎ ነው የታተመው። ስህተት ስለመሰለኝ ነው ያስተካከልሁት።

# የሞት ዓለም ሞት

ሰው ፤ ሰው መሆኑን ........
ሰው ፤ ሰው መሆኑን የሚያሳውቅ ከሆነ ፤ በጭካኔ ሞት
ኦ ! ሞት ስጠኝ እስከ ዘላለም- ሞት የሞት ሞት ::
ምን የህልፈተ ዓለም ጥሩንባ----ምን የጥፋት ከበሮ
ምን የክፋት ወጥመድ የቀጋ ሾህ፤ ዓለምን በሙሉ አስሮ
ምን ጩኸት ያሰማናል በየደቂቃው እርምጃ
ያቶሚክ ቦምብ ያዳፍኔ ...........
የተወሳሰበ ሙዚቃ ድምፅ ፤ የመትረየስ ወይ የጠመንጃ
የተጠላለፈ ሕይወት ሐረግ የመሠሪነት ሥጋጃ ::
ምን መርዝ የባብ ጭንቅላት !
የገበሎ ራስ ናዜራ ፤ የፉኝት ምራቅ ነቀርሳ
ምን ስራስር ያረግ ሬሳ !
ምን የምድር እምቧይ የጠጅ አሰር ፤
የድፍድፍ አንቃር ያተላ
ምን የደም እርሾ ኮምጣጣ ፤ የሚንተከተክ የሚፈላ ፤
ዋጊኖስ[1] እጸ ዘዌ[2] ፤ የፍልፈል አፈር ፈልፈላ !
ያንዱ ሞት የሌላው ሕይወት .............
ያንዱ መኖር የሌላው መጥፊያ ::
ጥሩ ሙዚቃ፤ ጥሩ ሙዚቃ ! ግሩም ማለፊያ፤ግሩም ማለፊያ

አቤት ! እግዚኦ ፤ አቤት !
ቪየትናም የቪየትናም ህልቂት[3] ፤ናጋሳኪ የሂሮሺማ መጥፋት
ሻርፐቪል--ሞት የሞት ሞት
የሬሳ ክምር መዓት !
የሰው ልጅ ጥፋት መቃብር ፤ የሰው ልጅ መኖር ወይ አለመኖር
የሰው ክፋት ትል የማይሞት ፤ የሰው ተንኮል መርዝ የማይበገር
ጥቁር ቀይ ፤ ቀይ ጥቁር ፤
ነጭ ጥቁር ፤ ብጫ ነጭ ቀይ ፤
ድብልቅልቅ ውጥንቅጥ ፤
ከሰማይ በታች ከመሬት በላይ ::
ያንዱ ሞት የሌላው ሕይወት...................
በግ ይታረዳል ሠንጋ ይጣላል የሠርግ ድግስ ዕልልታ
የደም ጠጅ መርዝ ስካር ፤ ከንቱ ሙዚቃ ኳኳታ
ከንቱ ያለም መሽከርከር ከንቱ ፤ የሌላው ዓለም ዓለም
ትቢያ የትቢያ ትቢያ--ኢምንት ቅንጣት ሰውር ፍጹም::
ሕይወት አበባ ጽጌረዳ ፤

---

[1] "ዋጊኖስ ፤ ... ሥሩና ፍሬው ለደም ለተቅማጥ መድኀኒት ይኾናል:: ቅጠሉም ቀጥቅጦ በውሃ ዘፍዝፎ ብልትንና ዐይንን እንዳይነካ ተጠንቅቆ ገላን ቢቀቡት ከዕከክ ያድናል:: ፪ኛ ስሙ ጉፋ ይባላል::" (ደስታ ተክለ ወልድ÷1962÷ ገፅ 411)
[2] "ዘዌ ፤ የዛፍ ስም፤ የመርዝ መድኀኒት የሚኾን ዕንጨት..." (ደስታ ተክለ ወልድ÷ 1962÷ ገፅ 482)
[3] "እልቂት" ማለቱ ነው::

ብርሃን ጭላንጭል ፍንጣቂ
የሞት እስትንፋስ ጠፊ ረቂቅ ፤ የሰባራ ገል ድቃቂ ::
ዓለም ሆይ ሒጂ ጥፊ ፤ ሒጂ መጥፎ ክፉ ዓለም
እንግዳ መሆኑን ያላወቀ ፤ እንግዳ መሆኑን ያጣው የለም
የለም ዘላለም በሰው ዘንድ ፤
ከንቱ ነው ሕይወት ዘላለም ::
የቴዎድሮስ ሞት መሥዋዕትነት !
አብርሃም ሊንከልን ፤ ማርቲን ሉተር ኪንግ ፤ ማህተማ
ጋንዲ ፤ ኬነዲ ደግሞ ኬኔዲ !
ብዙ ሰማዕታት ጠፍተው የቀሩት ፤
ብዙም ለውነት ማሰብ የሞቱት ::
አ ! ምን ድምፅ ያሰማናል ፤
ምን የጎግማጎግ ጩኸት ጋጋኖ !
ምን የምናምን ምናምን ፤ ሟርተኛ ደንቃራ ሆኖ
ምን የፍልፈል አፈር ፈልፈላ !
ምን የመቃብር አፈር ትኩስ ፤
የሙት አማጣኝ መንፈስ ሳቢ
የቤት ጥቀርሻ ጢስ ጠለሸት ፤ የምሰሶ እድፍ እጣቢ
ምን የሰው ክፋት መሠሪነት ፤ የሰው እርጉምነት አንደርቢ
ምን የሐሳብ ቅንቅን ስራይ ፤ የሕይወት ጥንጣን ነቀዝ
ምን ክፋት የኑሮ መተት ፤ የሰው ልጅ አንጠረፋ መሬንዝ
ዋጊኖስ እጸ ዘዌ !
የልቅሶ አስከሬን ዝንብ ሬሳ ፤ ሽረሪት ድርሳቅ ተከናንቦ
ያለም መጠንጠን ያለም መወዘግዘግ፤እምሀበ አልቦ ሀበ አልቦ ፤
ምን የጎግማጎግ[4] ጩኸት ጋጋኖ[5]
ምን የህልፈተ ዓለም ጥሩንባ !
ምን የሰው ሐዘን የሰው ጩኸት ፤
ምን ያዳም ልጅ ዘር የደም እንባ ::

---

[4] "ጎግ ማጎግ ፤ ጎግ ጀርመን ፤ ማጎግ መስኮብ:: ምሰጢሩ ብዛትንና አሕዛብነትን ያሳያል:: ጎግ ሕዝብ ፤ ማጎግ አሕዛብ ማለት ነው (ኪ ፡ ወ ፡ ክ):: ባላገር ግን ጉግ ማንጉግ ይላል::" (ደስታ ተክለ ወልድ÷ 19$2÷ ገፅ 229)::
[5] "ጋጋኖ... ርኩምና የወንዝ አመቴ መሳይ ፤ ያሞራ መንጋ በምድር በሰማይ የሚንጋጋ ፤ ጫኺ ድምጠ ረዥም ፤..." (ደስታ ተክለ ወልድ÷ ገፅ 229)::

# ለቡጊ

በግሬ ጣራ መርገጥ ፤
ሙዚቃ ሲጋልብ መውጣት መውረድ
መፍረጥ ፤
ዓይኔን ማገላበጥ ፤
መርበትበት መንቀጥቀጥ ፤
መላጋት መንገድገድ እንደሰከረ ሰው
የናፈቀኝ ይህ ነው ፤
ተነስቼ ልዝለል ፤
" ቡጊ ቡጊ " ልበል ::
ቡጊ ! ቡጊ ! ቡጊ !
ቡጊ ! ቡጊ ! ቡጊ !
ከበሮ ሲያጋፍት ጥሩንባ ሲያናፋ
ልብሴን ጥዬ ልጥፋ ::
ልራቆት አብጄ
ልብረር ካለም ሂጄ ::
ሙዚቃው በጥላው ይምጣ ይሸፍነኝ
ሁሉንም ያስረሳኝ ::
ቡጊ ቡጊ ልበል
እንደሳት ቡግ ቡግ
መውለብለብ መንተግተግ
መቃጠል መሞቅ ነው
ሲጀምር ሙዚቃው ::
ጉልበቴ ይላላል ፤ እግሬ መሬት ያካል ፤
ዛር ይሰፍርብኛል ::
ጅማቴ እየዛለ ይለቃል ሙላዬ ፤
አንገቴ ሲሰበር ወርዶ ትከሻዬ ::
ይረግጣል ዳንኪራ
ከከበሮው ጋራ
ቡጊ ! ቡጊ ! ቡጊ !
ልስበቀው ጀርባዬን ፤
ልወርውር እጆቼን ፤
ልመንጭር ጣቶቼን ፤
ሙዚቃን እንደ ኳስ ልለጋው በእግሮቼ
ልዝለል ተነስቼ ::
ልፍረጥ ፤ ልናር ፤ ልውደቅ ፤
መሬት ልንከባለል
ቡጊ ! ቡጊ ! ልበል ፤
ልዝለል ጮቤ ልምታ
ያቃዠኝ አንዳፍታ ::

# የጠፈር ባይተዋር

ግማሽ ቀልድ አላውቅም!
ሞት እንደሆን ልሙት በሲኮንድ መቶኛ
እንቅልፍ እንደሬሳ ዘላለም ልተኛ ::

መንገድ ስጡኝ ሰፊ ፣

ጉዞ ከጽንፍ አጽናፍ ፣
ፍጥነት እንደ ብርሃን ዓለማትን ልለፍ ::
ፀሐይ ልሁን ፀሐይ ፣
እንደ ጽርሐ አርያም[1] ሁሉንም የሚያሳይ ::
እሳተ ገሞራ አመድ እረመጡን ፣
ጎርፍ ፣ ሳት ጎርፍ ልሁን ::
ከሲኦል ሚሊዮን ቢሊዮን ልቃጠል ፣
ከገሀነመ እሳት ሚሊዮን ነበልባል ::

መንገድ ስጡኝ ሰፊ---

ልሒድ በጨለማ ዓይን የማያይበት ፣
ጥቁር የከሰለ ፣ በጠቆረው ጽልመት ፣
በጸጥታው ቦታ ዘመን ከቆመበት ::
በዘላለማዊው ባዶ ቦታ ዋሻ ፣
አየር በሌለበት አድማስ መጨረሻ ::

ልንሳፈፍ ልቃኘው ፣

ለኔ ኮከብ ጠጠር ኳስ መጫወቻ ነው ::

* ✱ *

ሰው ነው የረቀቀ !

ከሜርኩሪ ቪነስ ፣

ከጨረቃ ከማርስ ::

ከፐሉቶ ኔፐቱን ዑራነስ የላቀ ፣
ከጁፒተር ሳተርን ፀሐይ የደመቀ ፣
ባካባቢው ሁሉ እያሽበረቀ::

---

[1]"ጽርሐ አርያም ፣ በአርያም ያለ የብርሃን አዳራሽ:: አርያምን ተመልከት::" (ደስታ ተክለ ወልድ÷ 1962÷ ገፅ 1020):: "አርያም ፣ የሰማይ ስም ፣ መጨረሻ ሰማይ:: ዘሩ በግእዝ ረዱም ሬመ ነው::" (ደስታ ተክለ ወልድ÷ ገፅ 137)::

ሰው አደገ አወቀ ፤
መሬት ዕንቁላሉን ሰበረ መጠቀ ።
ሰው ዓለምን አየ !
በጨለማው ቦታ ዶቃ አንፀባራቂ ፤
ውብ ሰማያዊ ኳስ ፤ ውብ ሮዝ አብረቅራቂ ።
በተጣራው አየር በነጣው ደመና ፤
ባረንጓዴ እጣቢ ውሀ ተሸፍና ።
ውብ ሉል ኮከብ ዓለም ፤
የጠፈር ላይ ጤዛ ፤
የሰው ልጆች እናት ፤ የሰው ልጆች ቤዛ ።

* * *

የመሬት ቁራጭ ነኝ ፤
ታሪኳን የምጽፍ ፤
በጥቁር ወረቀት በሰማይ ብራና ፤
ስጓዝ እተዋለሁ በጠፈር ላይ ፋና ።
ስሔድ እኖራለሁ . . . . . . . . . . . . .
ሰማየ ሰማያት እመዘብራለሁ ፤
የተዘጋውን በር እበረግዳለሁ ።

የሌለ እስቲፈጠር ፤ የሞተ እስኪነቃ ፤
በትልቅ እርምጃ ከመሬት ጨረቃ ፤
ከጨረቃ ኮከብ ፤
ካንዱ ዓለም ወዳንዱ ፤
ስጓዝ እፈጥናለሁ . . .
በፀሐይ ላይ ቤቴን ጎጆ እቀልሳለሁ ።
ግማሽ ቀልድ አላውቅም !

ከሲኦል ሚሊዮን ቢሊዮን ልቃጠል ።
ከገሀነመ እሳት ሚሊዮን ነበልባል ።
መንገድ ስጡኝ - - -